www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.26
ADDIS ABABA 4th February, 2019

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፱/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ………………………ገጽ ፲ሺ፱፻፹

**Content**

Proclamation No.1109/2019

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda on Technical Cooperation in the Field of Agriculture Proclamation --………………………..Page 10980

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፱/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል በግብርና ዘርፍ ለመተባበር የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ ትብብር ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO.1109/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENTS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF RWANDA ON TECHNICAL COOPERATION IN THE FIELD OF AGRICULTURE.**

**WHEREAS,** the Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Rwanda on Technical Cooperation in the field of Agriculture has been signed in Addis Ababa, Ethiopia on the 5th day of June, 2013;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 10th day of January, 2019;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby Proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me



**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በግብርና ዘርፍ ለመተባበር የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፱/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በግብርና ዘርፍ ለመተባበር በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ የተደረገው ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. አስፈፃሚ አካላት**

ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅም ለግብርና ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda on Technical Cooperation in the Field of Agriculture Proclamation No. 1109/2019"

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement between The Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Rwanda on Technical Cooperation in the Field of Agriculture signed on the 5th day of June, 2013 in Addis Ababa, Ethiopia is hereby ratified.

**3. Implementing Organ**

The Ministry of Agriculture is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 4th day of February, 2019.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**